ህዳር 26/2004

ክቡር አቶ ገብረመስቀል ታረቀ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቃዊ ዞን አስተዳዳሪ

ክቡራን የሃይማኖት መሪዎች

ክቡራን የዓዲግራት ከተማ ነዋሪዎች

ክቡራን የተለያዩ ድርጅቶች ሃላፊዎችና ተወካዮች

የተከበራችሁ የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ መምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ክቡራን የተማሪዎች ቤተሰቦች እና

የተወደዳችሁ የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የመጀመርያ ተማሪዎች

በመጀመርያ ሁላችሁንም በዚህች ውብ በሆነችው የዓዲግራት ከተማ በዛሬው እለት ለምናደርገው ደማቅ የተማሪዎች አቀባበልና በአገራችን ለስድስተኛ ጊዜ ለሚከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን አከባበር ስነስርአት በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብና በራሴ ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ።

በጉጉት ስንጠብቀው የነበረው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እውን ሆኖ እነሆ ዛሬ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተናገድ ጀምሯል። የኢትዮጵያ መንግስት ትምህርትን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ፍትሃዊና ርትአዊ በሆነ መንገድ ለማዳረስ ባለው ቁርጠኛ እምነትና ተነሳሽነት ተገቢ እቅድ በመያዝ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ ዘንድሮ ስራቸውን ከጀመሩት ዘጠኝ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ተደምሮ በሀገራችን ያሉት ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር 31 አድርሶታል። ድህነትን ለማሸነፍ በሚደረገው ትንቅንቅ ትምህርት ቁልፍ መሳርያ መሆኑ እሙን ነው። የዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር መብዛት ብቻ ሳይሆን የቅበላ አቅማቸው በየጊዜው እያደገ መምጣቱ ያለውን የትምህርት ፍላጎት በማሟላት የአገራችን የእድገት ጉዞ አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያለው እንደሚያደርገው ይታመናል። በትምህርቱ ዘርፍ ባለፉት ጥቂት ሊባሉ በሚችሉ አመታት ውስጥ በጠቅላላ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሞያ ዘርፍ፣ እና በከፍተኛ ትምህርት የተመዘገበው ውጤት አገራችን እጅግ ኋላ ቀር ከነበረችበት ሁኔታ ወጥታ ወደ ተሻለ ደረጃ እንድትሸጋገር ያደረጋት መሆኑ ምስክር የማያሻ ጉዳይ ነው።

እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ1948 የታወጀው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ትምህርትን በተመለከተ በአንቀፅ 26 እያንዳንዱ ሰው የመማር መብት እንዳለው ያስቀምጥና የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም አስገዳጅ መሆኑን በመግለፅ ከፍተኛ ትምህርት ደግሞ ችሎታው ላለው ለሁሉም ሰው ተደራሽ መሆን አለበት ይላል። የከፍተኛ ትምህርት የተወሰኑና የታደሉ የህብረሰተሰብ ክፍሎች መጠቀምያ ሆኖ የቆየ ሲሆን ከዚህ ተላቆ ሁሉም በፍትሃዊነት የሚጠቀምበት መሆን ይኖርበታል። በዚህም መሰረት በአገራችን የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የብሄር፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ ወዘተ ልዩነት ሳይደረግበት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንዲሆን ታስቦ ነው ከተወሰኑ አመታት በፊት ሁለት ብቻ የነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች ወደ 31 እንዲያድጉ የተደገረው። ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲም ለዚህ የተቀደሰ አላማ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ ተመጣጣኝ ዝግጅቶችን በማድረግ ተማሪዎችን ለመቀበል ችላል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ግንቦት 18/2003 በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003 "ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ"

ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ሆኖ በከፍተኛ ትምህርት ኣዋጅ ቁጥር 650/2001 እንዲተዳደር የተቋቋመ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው። ዩኒቨርሲቲያችን አጀማመሩ መጠነኛ ቢሆንም ትልቅ ራእይ ሰንቆ ትላልቅ ስራዎችን ለመስራት ታጥቆ የተነሳ ተቋም ነው። ዩኒቨርሲቲው በማስተማር ስራ ብቻ ሳይሆን በምርምርና በህብረተሰብ አገልግሎት ለአከባቢው፣ ለአገሪቱና ከዚሁም አልፎ ለአለም ህብረተሰብ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት ከፍተኛ ፍላጎት፣ ተነሳሽነትና ዝግጁነት ያለው የትምህርት አውታር ነው።

የዩኒቨርሲቲው የህንፃ ግንባታ ስራ ከተጀመረ አንድ አመት ከስድስት ወር ያደረገ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ግንባታ በምእራፎች ተከፋፍሎ የሚከናወን ሆኖ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከ150 በላይ ብሎኮች ይኖሩታል። አሁን በመገንባት ላይ ያለው ክፍል የመጀመርያው ምእራፍ ሲሆን የመጀመርያው ምእራፍም ራሱ በሁለት ክፍሎች ተከፋፍሎ በመከናወን ላይ ይገኛል። የመጀመርያው ምእራፍ አንድ አራተኛው ክፋይ 12 ብሎኮችን የያዘና በአሁኑ ሰአት የተጠናቀቀው የግንባታው ክፍል ነው። የዚሁ የመጀመርያው ምእራፍ ሶስተ አራተኛው ክፋይ ደግሞ 36 ብሎኮችን የያዘ ሲሆን የግንባታው 60 ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪው በሚቀጥሉት ወራት የሚጠናቀቅ ይሆናል። ከህንፃ ግንባታ ስራዎች በተጨማሪ የውሃና ፍሳሽ፣ የመብራት፣ እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ስራዎችን የሚያጠቃልለው የመሰረተ ልማት ግንባታም በምእራፎች ተከፋፍሎ የሚከናወን ሆኖ የመጀመርያው ምእራፍ 65 ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪውና በዋናነት የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ስራን የሚያካትተው ክፍል በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ተሰርቶ የሚጠናቀቅ ይሆናል። የሁለተኛው ምእራፍ የህንፃና የመሰረተልማት ግንባታ ደግሞ በቅርቡ እንደሚጀመር ይጠበቃል። በዚህ አኳሃን የግንባታው ስራ ከትምህርቱ ስራ ጎን ለጎን የሚቀጥል ይሆናል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ሁለት ግቢዎች ያሉት ሆኖ ኣጠቃላይ የመሬት ስፋቱ ደግሞ 160 ሄክታር ነው። አንደኛው ግቢ አሁን ያለንበት ዋናው ግቢ ሲሆን የመሬት ስፋቱ 100 ሄክታር ነው። ሁለተኛው እና 60 ሄክታር የመሬት ስፋት ያለው ግቢ ደግሞ በከተማው ምእራብ አከባቢ የሚገኘው ሆኖ እስካሁን የግንባታ ስራ ኣልተጀመረበትም። ዩኒቨርሲቲያችን ከኣዳዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን በማስተናገድ ኣቅሙ በኣዲስ ኣበባ ከተቋቋመው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚመደብ ሲሆን በኣምስት ኣመታት ውስጥ የሚኖሩት የተማሪዎች ብዛት 15 ሺህ ያህል ሊደርስ ይችላል በሚል ታሳቢ ነው በመሰራት ላይ የሚገኘው።

ዘንድሮ የተቀበልናቸው ተማሪዎች ብዛት 960 ሲሆን ተማሪዎቻችን ከመላው የአገሪቱ ክልሎችና ክፍሎች የተውጣጡ ናቸው። ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ከተመደቡት የመጀመርያ ተማሪዎች ውስጥ 65 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ በፍጥነት እያደገ መሆኑ አመላካች ነው። በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ፕላኑ የተያዘው የሴቶች ተሳትፎ የማሳደጉ ታርጌት የሚደረስበት መሆኑም የሚያሳይ ነው። ዓዲግራት ከተማም እነዚህን ተማሪዎች ለማስተናገድ የታደለች በመሆንዋ ከፍተኛ ደስታ እንደሚሰማት የሚያጠራጥር አይደለም። በከፍተኛ ጉጉት ስትጠብቀው የነበረች መሆንዋም እናውቃለን። የከተማው ህዝብና አስተዳደር ባለፉት ሁለት ቀናት ተማሪዎችን ለመቀበል ባሳየው ትጋትና አስተዋፅኦ ደስተኝነቱን በተግባር ገልፆልናል። ተማሪዎቻችንም የዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ እና የአከባቢው ህዝብ በጣም እንደሚወዳችሁ ተገንዝባችሁ እናንተም አፀፋውን ለመመለስ መዘጋጀት ይጠበቅባቹሃል፣ በትምህርቱም፣ በስነምግባሩም፣ እርስ በርስ ተከባብሮና ተሳስቦ በመኖሩም። ከቤተሰብ ለመጀመርያ ጊዜ ተለይቶ መምጣት የራሱ የሆነ ናፍቆት የሚያስከትል መሆኑ የሚታወቅ

ቢሆንም የመጣችሁት ወደ ሌላ ቤተሰባችሁ መሆኑ ልታውቁት ይገባል። የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የመጀመርያ ተማሪዎች በመሆናችሁና የዚህ ትልቅ ታሪክ አካል በመሆናችሁ ከፍተኛ ደስታ ሊሰማችሁ ይገባል። ቢያንስ ቢያንስ ፍሬሽ ብሎ የሚሳለቅባችሁ ሌላ ተማሪ አሁን የለም። እንግዲህ እናንተ በሚቀጥለው አመት ለምንቀበላቸው በርከት ያሉ ተማሪዎች እንዴት እንደምታስተናግዱዋቸው ያኔ እናያለን። የዩኒቨርሲቲ ህይወት በትምህርት ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ኑሮም ከፍተኛ ልምድ የሚቀሰምበት ቦታ ነው። ሲጀመር ልብ ባር ባር ይላል ቀስ ብሎ ሲለመድ ግን ይጥምና መለየቱ ያስቸግራል። የራሱ ታሪክ ያለው ትልቅ የህይመት ምእራፍ ይሆናል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የተቀበለው በአራት ባንዶች ነው፤ ባንድ አንድ /ምህንድስና/፣ ባንድ ሁለት /የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ/፣ ባንድ አምስት /ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ/፣ እና ባንድ ስድስት /ማህበራዊ ሳይንስ/ ናቸው። በየባንዱ የተቀበልናቸው ተማሪዎች ብዛት ደግሞ በምህንድስና 404 ተማሪዎች፣ በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ 263 ተማሪዎች፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ 192 ተማሪዎች እና በማህበራዊ ሳይንስ 101 ተማሪዎች ናቸው። የአመዳደብ ስብጥር በተመለከም ከጠቅላላው ተማሪዎች 69.5 ከመቶ የሚሆኑት በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ የተመደቡ ሲሆን የተቀሩት 30.5 ከመቶ በማህበራዊ ሳይንስ መስክ የተመደቡ ናቸው። ስለዚህ አመዳደቡ አገሪቱ የምትከተለውን የ70 - 30 ስብጥር ከወዲሁ ያሟላ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ቀጥሎ መሰራት ያለበት ተማሪዎች በየትምህርት ክፍሉ የመመደቡ ጉዳይ ይሆናል። በዚሁም መሰረት ተማሪዎቻችን በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት በሚከተሉት ትምህርት ክፍሎች የሚመደቡ ይሆናሉ፤

- በምህንድስና መስክ ስር /ኤሌክትሪካል ምህንድስና፣ ሜካኒካል ምህንድስና ሲቪል ምህንድስና እና ኬሚካል ምህንድስና/
- በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ መስክ ስር /ስነህይወት ወይም ባዮሎጂ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ እና ሂሳብ/
- በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ መስክ ስር /አካውንቲንግና ፋይናንስ፣ ኢኮኖሚክስ እና ማኔጅመንት/
- በማህበራዊ ሳይንስ መስክ ስር /እንግሊዝኛና ስነጼጋና ስነምግባር/

የሰው ሃይልን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ጊዜ 96 መምህራንና 175 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት። በሲቪልና በኬሚካል ምህንድስና የመምህራን እጥረት ያለን ቢሆንም በሌሎች መስኮች ግን ለዘንድሮ በቂ መምህራን አሉን። ዩኒቨርሲቲው ከላይ ከተጠቀሱት ባንዶች በተጨማሪ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን በጤና ሳይንስና በግብርና መስኮች ትምህርት ለመጀመር ዝግጅቶችን ከወዲሁ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚሁም በተጨማሪ በሚቀጥለው አመት ዘንድሮ በጀመርናቸው ባንዶችም ተጨማሪ ትምህርት ክፍሎችን ይከፍታል። የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅጥርም በመቀጠል ላይ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲያችን የአመቱ ሰራ የጀመረው ነባር ዩኒቨርሲቲዎች በመተግበር ላይ ያሉት የተቋማዊ ለውጥ እና የመልካም አስተዳደር ሰራዎችን በመንተራስ ወደፊት መቀጠል በሚል መርህ ሲሆን ተማሪዎቻችን በተለያዩ ስራዎች ውስጥ በስፋት የሚሳተፉበት አሰራር እንከተላለን። ይህ መርህ በካሪከለም፣ በማስተማር፣ በምዘና፣ በድጋፍ አሰጣጥ ወዘተ… የምንከተለው ይሆናል። ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ አቅማችንን አሰባስበንና

አሚጠን የምንሰራ ሲሆን መሟላት ያለባቸው ነገሮች ደግሞ በሂደት የሚሟሉበት አሰራር እንከተላለን።

ዘንድሮ በፕላን ከያዝናቸው ነገሮች ወስጥ አንዱ የዩኒቨርሲቲውን ግቢ በተክል የማስዋብ ሰራ ሲሆን ተማሪዎቻችን እንዲሁም መላው መምህራንና ሰራተኞች በንቃት እንዲሳተፉ እንፈልጋለን። በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የአከባቢው ተወላጆችም ሆነ ሌሎች ድጋፍ ሊያደርጉልን የሚፈልጉ በተለይ በመፃህፍት እና በመላው አለም ጋር ከሚገኙ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ትብብራቸው እንዳይለየን በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ለማቅበር እንወዳለን።

ዛሬ የምናከብረው በአል አዲስ ተማሪዎችን የመቀበል ብቻ ሳይሆን በተጓዳኝ ለስድስተኛ ጊዜ የምናከብረውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን እዚህ ዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ የምናከብርበት አጋጣሚም ነው። አገራችን የፌደራላዊ ስርአት መከተል ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በሃገሪቱ የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልዩኒታችን ውበታችን ነው በሚል መርህ ልዩነታችንን አክብረን ተፈቃቅረንና ተፈቃቅደን የምንኖርበትና አንድነታችንን የምናጠናክርበትና የምናጎለብትበት እድል ፈጥሮልናል። አገራችን እያስመዘበችው ላለችው ሁሉን አቀፍ እድገትና ልማት መሰረቱ ህገመንግስቱና የፌደራል ስርአቱ ስለሆነ ህገመንግስታችን ለብዙህነታችን፤ ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን በሚል መሪ ቃል የምናከብረው የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን በዩኒቨርሲቲያችን ዛሬ ስናከብረው በታላቅ ድምቀትና የእርካታ መንፈስ ነው።

በመጨረሻም ይሄንን ዛሬ በማክበር ላይ ያለነውን ድርብ በአል ለማዘጋጀት የተደረገው ድርብርብ ጥረት ሳላመሰግን ባልፍ /አምስጋኝና ተመስጋኝ ማስቀመጡ አስቸጋሪ ቢሆንም/ የተሰራውን ስራ ክብደት መቀነስ ሆኖ ሊያስቆጥርብኝ ይችላል። በዚሁም መሰረት ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ካሉት አካላት ብጀምር የክልሉ አስተዳደር፤ የዞኑ አስተዳዳሪ ፅ/ቤት፤ የዓዲግራት ፓሊቴክኒክ ኬሌጅ፤ የአግአዚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የዓዲግራት ከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት ይህ ቀረሽ የማይባል ድጋፍ ስላደረጉልን ምስጋናዬን በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እና በራሴ ስም አቀርባለሁ። የዓዲግራት ቤቶች ልማት ኤጀንሲ ሰራተኞች እንዲሁም የግንባታው ኮንሳልታንቶችና ኮንትራክተሮች በሙሉ በጣም እያመሰገንኩኝ በተለይም ደግሞ አቶ ነጋሽ አርአያ የተለየ ምስጋና ብንቸራቸው የሚያንሳቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይሆንም። የትምህርት ሚኒስቴር፤ መቐለ ዩኒቨርሲቲ እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ላደረጉልን ድጋፍ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ደግሞ ከዘበኛ እስከ ሃላፊ፤ ከፅዳት እስከ መምህር ያለውን በሙሉ ሳይቆጥብ በራሱ ተነሳሽነት ሲያስፈግ በማስተባበር አልያም በቀጥታ በጉልበት በብርሃንም ይሁን በጨለማ ተረባርቦ ባይሰራ ኖሮ እዚህ ላይ መድረስ አይቻልም ነበር። ይህ ልዩ የሆነ የአንድነት መንፈስ የተንፀባረቀበት አጋጣሚ ስለነበረ የዩኒቨርሲቲው አመሰራረት ታሪክ ቋሚ አካል ሆኖ ለዘልአለም ይኖራል።

አመሰግናለሁ!!!